**የጥናት ክፍል፡** ሐዋርያት 8፡1-25

**ርዕስ፡** ወንጌል ከኢየሩሳሌም ወደ ይሁዳና ሰማርያ መስፋፋት (ሐዋ 1፡8)

**መግቢያ፡-**

የእስጢፋኖስ ሰማዕትነትን ተከትሎ በኢየሩሳሌም በነበረችው ቤተ ክርስቲያን ላይ ትልቅ ስደት ሆነ፡፡ በየሩሳልም የነበሩት ወደ ተለያዩ ሀገሮች ተበተኑ፡፡ ፊልጶስ ወደ ሰማርያ ወረዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው ድንቅና ምልክት ይደረጉ ስለነበር የሰማርያ ሰዎች ጠንቋዩም ሲሞን ጨምሮ ብዙ ሰዎች አምነው ተጠመቁ፡፡ በየሩሳሌም የነበሩ ሐወሪያት ይህንን ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሃንስን ላኩላቸው፡፡ ዮሃንስና ጴጥሮስም ወደ ሰማሪያ መጥተው እጃቸውን ሲጭኑባቸው የሰማሪያ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው፡፡ ሲሞንም የህንን ባየ ጊዜ ገንዘብ አምጥቶላቸው የእግዚአብሔርን ስጦታ መግዛት ፈለገ፡፡ ጴጥሮስ ግን ንስሃ እንዲገባ አጥብቆ ገሰፀው፡፡

I. የንባቡን ክፍል ዋና ታሪክ ለቡድን አባላት ግለፅ (Head)

የመወያያ ጥያቄዎች

1. ለወንጌል ከየሩሳሌም ዉጭ መስፋፋት ዋና ምክንያት ምን ነበር?
2. በሰማሪያዊያንና በአይሁዶች መካከል የነበረው ልዩነት አብራ

   የሰማሪያ ሰዎች አማጣጥ ታሪክ 2 ነግስት 17:1-41)

3. የፊልጶስና እስጢፋኖስ አገልግለት ምን ያመሳስላቸዋል ? (ሐዋ 6፡5)

4. የፊልጶስ ዋና የስብከት ርዕስ ስለ ምን ነበር?

5. ሲሞን ትክክለኛ አማኝ ነበር? (አምኗል ተጠምቋል)

6. በሲሞንና በፊልጶስ የሚደረጉ ታምራት መካከል ምን ልዩነት አለ?

7. የሲሞን ዋና የልብ ፍላጎት ምን ነበር?

8. ዛሬ የሚደረጉትን ታምቶች ከጌታ ይሁን ከአጋንንት ይሁኑ እንዴት መለየት ይቻላል?

II. ከክፍሉ እግዚአብሔር ለግልህ ያስተማረህን ለቡድን አባላት ተናገር (Heart)
III. ዛሬ መንፈስ ቅዱስ ከተናገረን ውስጥ ልንተገብራቸው የሚገቡን ምን ምን ናቸው (Hand)